# የ DDC የአምስት ዓመት የግዛት ዕቅድ 2022-2026 ረቂቅ ቨርቹዋል ሕዝባዊ ችሎቶች እና የ 45 ቀን የሕዝብ አስተያየት መቀበያ ጊዜ (እንግሊዝኛ)

(The DDC Five-Year State Plan 2022-2026 Draft, Virtual Public Hearings, and 45-Day Public Comment Period – Amharic language)

የኮሎምቢያ ዲስትሪክት ዕድገታዊ አካል ጉዳተኝነት ካውንስል (DDC) ለ 2022–2026 የበጀት ዓመታት የሚሆን አዲስ የአምስት ዓመት የግዛት ዕቅድ ለማዘጋጀት በሒደት ላይ ነው። የግዛት ዕቅዱ የ DDC የወደፊት አቅጣጫና ግቦችን የሚመራ ሲሆን፣ የማህበረሰቦችን የተለያዩ ድምፆችንም ያንጸባርቃል።

የ DDC የአምስት ዓመት የግዛት ዕቅድ 2022-2026 ረቂቅ ግቦች፣ ዓላማዎችና ቅድሚያ የሚሰጣቸው ጉዳዮች ለ 45 ቀናት ያህል የሕዝብ አስተያየት ይሰጥባቸዋል። የ DDC የግዛት ዕቅድ ዋና ግቦች የራስን ዕድል በራስ የመወሰን፣ ተሟጋችነትና አመራር፣ የስራ ቅጥር እና የማህበረሰብ አኗኗር ናቸው። ሌሎች አጽንኦት ከሚሰጣቸው መስኮች መካከል ትምህርት፣ መኖሪያ ቤት፣ ጤና እና መደበኛ እና ኢ-መደበኛ የማህበረሰብ ድጋፍ ይገኙበታል። ረቂቅ ዕቅዱን እዚህ ላይ ማግኘት ይቻላል፡ https://ddc.dc.gov/page/2022-2026-state-plan

የ DDC የአምስት ዓመት የግዛት ዕቅድ 2022-2026 የ45 ቀናት የሕዝብ አስተያየት መስጫ ጊዜ የሚጀምረው ሜይ 5/2021 ሲሆን የሚቆየውም እስከ ጁን 18/2021 ድረስ ነው።

እርስዎ በረቂቅ ዕቅዱ ላይ ግብረ መልስዎን የሚሰጡባቸው የተለያዩ መንገዶች አሉ፡

1. ሐሙስ፣ ሜይ 27/2021 ከ10:00 AM እስከ 11:00 AM እና ከ 1:00 PM እስከ 2:00 PM ከሚካሄዱት ሁለት የቨርቹዋል ሕዝባዊ ስብሰባዎች በአንዱ መሳተፍ። አስቀድመው እዚህ ይመዝገቡ፡ https://ddc.dc.gov/page/2022-2026-state-plan
2. የሕዝብ አስተያየት መሰብሰቢያ የዳሰሳ ጥናታችንን በቀጥታ ይሙሉ። በእንግሊዝኛ፣ ስፓኒሽ፣ አማርኛ፣ ኮሪያኛ፣ ቬትናምኛ፣ ቻይንኛ እና ፈረንሳይኛ የተዘጋጀው የዳሰሳ ጥናታችን ማስፈንጠሪያ እዚህ ይገኛል፡ https://ddc.dc.gov/page/2022-2026-state-plan
3. አስተያየቶችዎን በዚህ የኢሜይል አድራሻ ይላኩ፡ ddcstateplan.comments@dc.gov
4. አስተያየቶችዎን በቀጣዩ የፖስታ አድራሻ ይላኩ፡ Developmental Disabilities Council, 441 4th Street, NW, Suite 729N, Washington, DC 20001

ግብረ መልስዎን ለመስጠት ድጋፍ ወይም መስተንግዶ ካስፈለገዎት፣ እባክዎ ለ Alison Whyte በኢሜይል alison.whyte@dc.gov ወይም በስልክ ቁጥር 202-340-8563 ይደውሉ ወይም መልእክት ይላኩ።

የኮሎምቢያ ዲስትሪክት ዕድገታዊ አካል ጉዳተኝነት ካውንስል (DDC) በዲሲ ውስጥ የሚኖሩና ዕድገታዊ አካል ጉዳት ያለባቸው ሰዎችና ቤተሰቦቻቸው የበለጠ ነጻነት፣ አካታችነት፣ ማብቃትና በመረጡበት መንገድ ሕይወትን እንዲቀጥሉ ድምጻቸውን ለማጠናከር ይፈልጋል። በሙብት መሟገታችን አማካይነት አድልዎን ለማስቀረትና የሙሉ አካታችነት እንቅፋቶችን ለማስቀረት የሚያስችል ለውጥ ለመፍጠር እንተጋለን። DDC የተቋቋመውና የሚንቀሳቀሰው በ Developmental Disabilities Assistance and Bill of Rights Act of 2000 (DD Act) Public Law 106-402 ነው።

# የዲሲ ዕድገታዊ አካል ጉዳተኝነት ካውንስል የአምስት ዓመት የግዛት ዕቅድ
# እንደ ሃሳብ የቀረቡ ግቦችና ዓላማዎች
# የሒሳብ ዓመት 2022-2026

## በስራችን ላይ ተጽእኖ የሚያሳድሩ እሴቶች

ብዝሃነት፣ ርቱዓዊነትና አካታችነት
ባሕላዊና የቋንቋ ብቃት
ሰውን ያማከለ አስተሳሰብ
ማሕበራዊ ፍትሕ እና ትስስር
ሰብአዊና የሲቪል መብቶች
አመራር እና ተሟጋችነት
ትብብር

## ግብ 1፡ የራስን ዕድል በራስ መወሰን፣ ተሟጋችነት እና አመራር

እ.ኤ.አ. ሴፕቴምበር 2026 በዲሲ ውስጥ የሚኖሩ ዕድገታዊ አካል ጉዳተኞች እና ቤተሰቦቻቸው፣ እንዲሁም የተለያየ የባሕል ማንነት ያላቸውን ጨምሮ፣ ሀ) የራስን ዕድል በራስ የመወሰን፣ የተሟጋችነት እና የአመራር ዕውቀት እና ክህሎታቸውን እና ለ) ለፖሊሲ አውጪዎች ስለርቱዓዊነት እና ስለመደመር የማስተማር አቅማቸውን ያሳድጋሉ።

### ዓላማ 1

እ.ኤ.አ. ሴፕቴምበር 2026 DDC የሚከተሉትን ሁሉ ያከናውናል፡ (ሀ) ዕድገታዊ አካል ጉዳተኞች የሚመሩት ቢያንስ አንድ የራስ-ተሟጋች ድርጅት ያጠናክራል፣ (ለ) የራስ ተሟጋች መሪዎች የተለያየ የባሕል ማንነት ላላቸውና መሪ ሊሆኑ ለሚችሉ ለሌሎች ዕድገታዊ አካል ጉዳተኞች ስልጠና እንዲሰጡ የተደገፉ አጋጣሚዎች ይኖራቸዋል እና (ሐ) ዕድገታዊ አካል ጉዳተኞች በተለያየ የአካል ጉዳት ዘርፍ፣ በባህል የተለያየ አመራር እና በተሟጋችነት ቅንጅቶች ውስጥ የሚኖራቸው ተሳትፎ ድጋፍና ማስፋፊያ ይደረግላታል። ይህ ዓላማ ዕድገታዊ አካል ጉዳት ያለባቸው ሰዎች በመብት ተሟጋችነት ተግባራት እና በአመራር ቦታዎች ላይ የሚኖራቸውን ተሳትፎ የሚያሳድግ ሲሆን በዚህ ምክንያት ደግሞ አካታች የሆኑ ማህበረሰቦችን ለመገንባተ የሚያስችሉ አገልግሎቶችና ድጋፎች ዝግጅትና ተደራሽነት ላይ ተጽእኖ ያሳድራሉ። DDC ይህ ዓላማ የሚያሳካው ከዕድገት የአካል ጉዳት ኔትወርክ አጋሮች (Georgetown University Center for Excellence in Developmental Disabilities (GUCEDD) and Disability Rights DC at University Legal Services (P&A) ጋር በመተባበር ነው። *(ቢያንስ 5 ድርጅቶች በትብብር ስራው ውስጥ እንደሚሳተፉና ቢያንስ 150 ግለሰቦችም በአምስት ዓመቱ ዕቅድ ውስጥ በዚህ ተግባር ውስጥ ተሳታፊና ተጠቃሚ እንደሚሆኑ ይገመታል*

### ዓላማ 2

እ.ኤ.አ እስከ ሴፕቴምበር 2026 ድረስ DDC በቤተሰብ ተሳትፎ፣በባሕልና በቋንቋ ረገድ ብቁ የሆኑ መርጃዎች እና መረጃዎች የተሻሻሉ ተደራሽነት ስልጠና በመስጠት ከላቲኖ እና ከሂስፓኒክ ማህበረሰብ ውስጥ ዕድገታዊ አካል ጉዳት ያለባቸውን

ሰዎች ዕውቀትና ተሳትፎ ያሳድጋል። ይህን ዓላማ ለማሳካት በላቲኖ እና በሂስፓኒክ ማህበረሰብ ጥንካሬዎችና ፅናት ላይ እንመሰረታለን። ይህ ዓላማ የእውቀትና የአመራር ክህሎቶችን የሚያሳድግ፣ በስፓኒሽና በቀላል ቋንቋ የሚሰጥ መረጃን ተደራሽነት የሚያሳድግ፣ በአመራር ቦታዎች ላይ የሚሰሩ የላቲኖ እና የሂስፓኒክ ማህበረሰብ አባላትን ቁጥር የሚጨምርና በአጠቃላይ በዲሲ ማህበረሰቦች ውስጥ ርቱዓዊነትና አካታችነትን ለመገንባት በባልህና በቋንቋ ረገድ ብቁ የሆኑ ድጋፎችን ተደራሽነት ያሳድጋል። DDC ይህን ዓላማ የሚያሳካው ከዕድገት የአካል ጉዳት ኔትወርክ አጋሮች (Georgetown University Center for Excellence in Developmental Disabilities (GUCEDD) and Disability Rights DC at University Legal Services (P&A) ጋር በመተባበር ነው። *(ቢያንስ 5 ድርጅቶች በትብብር ስራው ውስጥ እንደሚሳተፉና ቢያንስ 50 ግለሰቦችም በአምስት ዓመቱ ዕቅድ ውስጥ በዚህ ተግባር ውስጥ ተሳታፊና ተጠቃሚ እንደሚሆኑ ይገመታል)*

**ዒላማ የተደረገ ልዩነት**፡ ስፓኒሽ ተናጋሪ ግለሰቦችና ቤተሰቦችን እና ድጋፍ ሰጪ ስርዓቶችን የማህበረሰቡን ጥንካሬና ፅናት በሚያከብርና የላቲኖ ማህበረሰቦችን ውስብስብ ፍላጎቶችና የቤተሰብ ተለዋዋጭ ባህርያት በሚያስተናግዱ መንገዶች ማሳተፍን አጽንኦት በመስጠት ዲሲ ውስጥ ለሚኖረው የላቲኖ ማህበረሰብ በባህልና በቋንቋ ብቁ የሆኑ አገልግሎቶች፣ ድጋፎችና መረጃ ተደራሽነት ላይ ያለውን ልዩነት መቀነስ።

### ዓላማ 3

እስከ ሴፕቴምበር 2026 ድረስ DDC ዕድገታዊ አካል ጉዳት ያለባቸው ሰዎችና የተለያዩ የባህል ማንነቶች ያላቸው ቤተሰቦቻቸው በአገልግሎቶችና ድጋፎች፣ በማሕበራዊ ፍትሕ ጅማሮዎችና ዕድገታዊ አካል ጉዳት ያለባቸው ሰዎችና ቤተሰቦቻቸው በማህበረሰቦች ውስጥ ተካታችነታቸውን የሚያሳልጡ ሌሎች ፖሊሲዎች ውስጥ ርቱዓዊነትን ለመደገፍ በፖሊሲ ውትወታ ተግባር ውስጥ የመሳተፍ አቅማቸውን እናሳድጋለን። በዚህ ዓላማ ምክንያትም በቂ መረጃ ያላቸውና ድጋፍ የሚያገኙ የአካል ጉዳተኞችና የቤተሰብ አባላቶቻቸው ተሟጋች ማህበረሰብ ይፈጠራል። DDC ይህን ዓላማ የሚያሳካው ከዕድገት የአካል ጉዳት ኔትወርክ አጋሮች (Georgetown University Center for Excellence in Developmental Disabilities (GUCEDD) and Disability Rights DC at University Legal Services (P&A)፣ ከሌሎች የማህበረሰብ ድርጅቶችና የማህበረሰበ መሪዎችና ተሟጋቾች ጋር በመተባበር ነው። *(ቢያንስ 3 ድርጅቶች በትብብር ስራው ውስጥ እንደሚሳተፉና ቢያንስ 50 ግለሰቦችም በአምስት ዓመቱ ዕቅድ ውስጥ በዚህ ተግባር ውስጥ ተሳታፊና ተጠቃሚ እንደሚሆኑ ይገመታል)*

---

## ግብ 2፡ የስራ ቅጥር

እስከ ሴፕቴምበር 2026 ድረስ DDC የስራ ቅጥር ላይ ካተኮሩ አጋሮች ጋር በትብብር በመስራት የስርዓት ለውጥ ለማምጣት የሚተጋ ሲሆን ይህም በሚከተሉት መንገዶች ለዕድገት አካል ጉዳተኞች እኩል የስራ ዕድሎችን ለማሳካት ጥረት የሚያደርግ ነው፡ ሀ) ማህበረሰቦችን በውድድር ላይ ስለተመሰረተና የተቀናጀ የስራ ቅጥር ማስተማር፤ ለ) አካል ጉዳተኞችን መቅጠር ስላለው ጠቀሜታዎች የማህበረሰቡንና የቀጣሪዎችን ግንዛቤ ማሳደግ፤ እና ሐ) አካታች የስራ አካባቢዎችና ይበልጥ ተወዳዳሪና የተቀናጁ የስራ ቅጥር ዕድሎችን ለማሳደግ የሚደረጉ ጥረቶችን መደገፍ።

### ዓላማ 1

እ.ኤ.አ. በሴፕቴምበር 2026 DDC ተቀማጭነታቸው በዲሲ ለሆነ አሠሪዎች እና ለዲሲ ማህበረሰቦች ዕድገታዊ አካል ጉዳተኞችን በተወዳዳሪነት፣ በተቀናጀ የሥራ ስምሪት አማካይነት መቅጠር የሚያስገኘውን ጠቀሜታ በተመለከተ ግንዛቤያቸውን ያሳድጋል፤ ለዚህም ከኤጀንሲዎች፣ ድርጅቶች እና አሠሪዎች ጋር በሚደረግ የትብብር ጥረት አማካይነት በቅድሚያ ቅጥር እና ተወዳዳሪ በሆነ የተቀናጀ የስራ ቅጥር ላይ ያተኮረ ባለብዙ መልክና ተቀያያሪ ስትራቴጂ ይጠቀማል። ይህም ዓላማ ይበልጥ አካታች የሆኑ አካባቢዎችን የሚፈጥር ሲሆን ዕድገታዊ አካል ጉዳት ያለባቸው ተጨማሪ ሰዎችም

በተቀናጁ ማዕቀፎች ውስጥ እንዲቀጠሩ ያስችላል። *(ቢያንስ 3 ድርጅቶች በትብብር ስራው ውስጥ እንደሚሳተፉና ቢያንስ 50 ግለሰቦችም በአምስት ዓመቱ ዕቅድ ውስጥ በዚህ ተግባር ውስጥ ተሳታፊና ተጠቃሚ እንደሚሆኑ ይገመታል)*

### ዓላማ 2

እ.ኤ.አ. እስከ ሴፕቴምበር 2026 DDC በኤጀንሲዎች መካከል በሚደረግ ትብብር አማካይነት በዲሲ መንግስት ውስጥ ዕድገታዊ አካል ጉዳት ላለባቸው ሰዎች ይበልጥ አካታች የሆኑ የስራ ዕድሎችን ለመፍጠር ቢያንስ አንድ ፖሊሲ እና ፕሮግራም የሚደግፍና የሚያበረታታ ይሆናል። ይህ ዓላማ ይበልጥ አካታች የሆኑ የስራ አካባቢዎችን የሚፈጥርና ዕድገታዊ አካል ጉዳት ያለባቸው ተጨማሪ ሰዎች በዲሲ መንግስት ውስጥ እንዲቀጠሩ ያስችላል። *(ቢያንስ 5 ድርጅቶች በትብብር ስራው ውስጥ እንደሚሳተፉና ቢያንስ 50 ግለሰቦችም በአምስት ዓመቱ ዕቅድ ውስጥ በዚህ ተግባር ውስጥ ተሳታፊና ተጠቃሚ እንደሚሆኑ ይገመታል)*

---

## ግብ 3፡ የማህበረሰብ አኗኗር

እ.ኤ.አ. እስከ ሴፕቴምበር 2026 ድረስ ዕድገታዊ አካል ጉዳተኞችና እና የተለያዩ ባህላዊ ማንነቶች ያሏቸው ቤተሰቦቻቸው በማህበረሰባቸው ውስጥ እንዲበለፅጉ የሚያስችሏቸውን ክህሎቶች፣ ሐብቶች እና ድጋፎች ያገኛሉ።

### ዓላማ 1

እ.ኤ.አ. እስከ ሴፕቴምበር 2026 ድረስ DDC ከግለሰብና ከቤተሰብ ተኮር አስተሳሰብ፣ ባህላዊና የቋንቋ ብቃትና አመራር ጋር ለተያያዙ ባለሙያዎች፣ እርዳታ ተቀባዮች፣ የማህበረሰብ ተሟጋቾችና ሌሎች ድርጅቶች የሚያገኙት መረጃ፣ ድጋፍና ስልጠና እንደዚሁም የቴክኒክ ስልጠና ተደራሽነት እንዲጨምር ያደርጋል። ይህ ዓላማ በግለሰብና ቤተሰብ ተኮር መርሆዎችና ባህላዊና የቋንቋ ብቃት ላይ የተመሰረቱ ስርዓቶችና ፕሮግራሞችን እንደዚሁም ርቱዓዊነት፣ ማሕበራዊ ፍትሕንና ዕድገታዊ አካል ጉዳተኞችና ቤተሰቦቻቸው በማህበረሰቡ ውስጥ የሚኖራቸውን ተካታችነት የሚያሳድጉ የማህበረሰብ መሪዎችን ያስገኛል። DDC ይህን ዓላማ የሚያሳካው ከዕድገት የአካል ጉዳት ኔትወርክ አጋሮች (Georgetown University Center for Excellence in Developmental Disabilities (GUCEDD) and Disability Rights DC at University Legal Services (P&A) ጋር በመተባበር ነው። *(ቢያንስ 3 ድርጅቶች በትብብር ስራው ውስጥ እንደሚሳተፉና ቢያንስ 100 ግለሰቦችም በአምስት ዓመቱ ዕቅድ ውስጥ በዚህ ተግባር ውስጥ ተሳታፊና ተጠቃሚ እንደሚሆኑ ይገመታል)*

### ዓላማ 2

እ.ኤ.አ. እስከ ሴፕቴምበር 2026፣ DDC የስጋት ክብርን በሚገነዘቡ እና ደህንነታቸው የተጠበቀ ልምዶችን በሚያመጣጥኑ መንገዶች ጤናማ የሰዎችን የእርስ በርስ ግንኙነትን (ማህበራዊ፣ ሙያዊ፣ የቅርብ እና/ወይም ወሲባዊ) ለመዳሰስ እና ለማዳበር የሚያስችሉ ተግባራት እና ፕሮግራሞችን ይደግፋል። ይህ ዓላማ ዕድገታዊ አካል ጉዳት ያለባቸው ሰዎችና የተለያዩ ባህላዊ ማንነቶች ያላቸው ቤተሰቦቻቸው የእርስ በርስ ግንኙነቶች ውስጥ ለመሳተፍ እና ለመደገፍ እንዲሁም ለህብረተሰቡ ካለን እይታ አንጻር እነዚህን ግንኙነቶች ለመቀበል እና ለማካተት የባህላዊ ለውጥ እንዲኖር አስተዋፅኦ ለማበርከት የሚያስችላቸው እውቀት፣ ችሎታና ክህሎት እንዲጨምር ያደርጋል። *(ቢያንስ 3 ድርጅቶች በትብብር ስራው ውስጥ እንደሚሳተፉና ቢያንስ 100 ግለሰቦችም በአምስት ዓመቱ ዕቅድ ውስጥ በዚህ ተግባር ውስጥ ተሳታፊና ተጠቃሚ እንደሚሆኑ ይገመታል)*

## ዓላማ 3

እ.ኤ.አ. በ 2026፣ DDC ዕድገታዊ አካል ጉዳተኞችና የተለያየ ማንነቶች ያላቸው ቤተሰቦቻቸው በሕይወት ኡደታቸው ውስጥ የአገልግሎትና የድጋፍ ሽግግሮችን ተገንዝበው እንዲፈትሹ የሚያስችል አቅማቸውን ያሳድጋል፤ ይህም የመማር አካል ጉዳት ያለባቸው ሰዎች ሕግ (IDEA) ክፍል ሲ ወደ ክፍል ቢ መሸጋገር፣ ሁለተኛ ደረጃ ሽግግርና የጤና እንክብካቤ ሽግግሮች ይገኙበታል። ይህ ዓላማ በእያንዳንዱ የሽግግር ወቅት ላይ ለሚያስፈልግ ነገር በሚገባ ለመሟገት የሚያስፈልግ እውቀት፣ ችሎታና ክህሎቶች እንዲጨምሩ ያደርጋል። DDC ይህን ዓላማ የሚያሳካው ከዕድገት የአካል ጉዳት ኔትወርክ አጋሮች (Georgetown University Center for Excellence in Developmental Disabilities (GUCEDD) and Disability Rights DC at University Legal Services (P&A) ጋር በመተባበር ነው። *(ቢያንስ 3 ድርጅቶች በትብብር ስራው ውስጥ እንደሚሳተፉና ቢያንስ 75 ግለሰቦችም በአምስት ዓመቱ ዕቅድ ውስጥ በዚህ ተግባር ውስጥ ተሳታፊና ተጠቃሚ እንደሚሆኑ ይገመታል)*

## ዓላማ 4

እ.ኤ.አ. ሴፕቴምበር 2026 ላይ DDC ዕድገታዊ አካል ጉዳተኞችና የተለያዩ ማንነቶች ያላቸውን ጨምሮ ቤተሰቦቻቸው ለአካል ጉዳተኛ ማህበረሰብ ክብር በሚሰጡና የተለያዩ የሲቪክ ተሳትፎ አጋጣሚዎችን በሚደግፉ የቴክኖሎጂ እና የግንኙነት ስትራቴጂዎችን በመጠቀም ከማህበረሰቦቻቸው ጋር የመገናኘት አቅምን ያሳድጋል። ይህ ዓላማ ዕድገታዊ አካል ጉዳተኞችና ቤተሰቦቻቸው የማህበረሰቦቻቸው የማይነጣጠሉ አባላት በመሆን ሙሉ ሕይወትን ይኖሩ ዘንድ እንቅፋቶቻቸው እንዲቀንሱ ያደርጋል። *(ቢያንስ 5 ድርጅቶች በትብብር ስራው ውስጥ እንደሚሳተፉና ቢያንስ 100 ግለሰቦችም በአምስት ዓመቱ ዕቅድ ውስጥ በዚህ ተግባር ውስጥ ተሳታፊና ተጠቃሚ እንደሚሆኑ ይገመታል)*

## ዓላማ 5

እ.ኤ.አ. ሴፕቴምበር 2026 ላይ DDC በዲሲ ውስጥ ዕድገታዊ አካል ጉዳት ላለባቸው ተመጣጣኝና ተደራሽ የሆኑ የመኖሪያ ቤት አማራጮችን በተመለከተ የመረጃ መሰናክሎችን ለመቀነስ እና በኤጀንሲዎች መካከል የሚደረግ ትብብርን የሚያካትት ቢያንስ አንድ ፖሊሲ ወይም ፕሮግራም ይደግፋል። ይህ ዓላማ ለተመጣጣኝና ተደራሽ መኖሪያ ቤት ተሟጋችነት የባለድርሻ አካላት ተሳትፎ እንዲጨምር ያደርጋል። *(ቢያንስ 2 ድርጅቶች በትብብር ስራው ውስጥ እንደሚሳተፉና ቢያንስ 25 ግለሰቦችም በአምስት ዓመቱ ዕቅድ ውስጥ በዚህ ተግባር ውስጥ ተሳታፊና ተጠቃሚ እንደሚሆኑ ይገመታል)*